

ለብዙ ዓመታት በረቀቀ አስተሳሰብ የሀገር፣ የወገን እና የቅርሳችን መከበርና መጠበቅ፣ በሀብት በበጎ አስተዳደር መካብና መበልጸግ ጥሩ አማራጭ መንገዶችን በማስተጋባት የኢትዮጵያ ኃያል ድምጽ በመሆን ሀገሩንና ወገኖቹን በቆራጥነት አገልግሏል።

በጽሑፎቹ ሁሉ እነዚህን መልዕክቶች የጤናው መቃወስ ሳያግደውና ሳያቋርጥ በማስተላለፍ ከጸና ዕምነቱ እጥፍ ወይም ገደል ሳይል ለወገኖቹ መልካም አርአያ ሆኖ ቆይቷል።

ወንድም ወልደአማኑኤል ኢ.ኢ..ድ.ኤን በተባለው ድረገጽ መድረክ የኢትዮጵያኖች መልከ ምግባር ውይይት እጅግ የታወቀና የተከበረ ተሳታፊ ነበር። የወንድማችን መለየት ታላቁን የኢትዮጵያ ድምጽ እንድናጣ አርጎናል።

ወንድም ወልደአማኑኤል ቢለየንም የሚረሳ አይደለም። በጓደኞቹና በወገኖቹ ህሊና ምንጊዜም ሲታወስ ይኖራል። ስሙም ለኢትዮጵያ ከተሰውት አርበኞች ስም ዝርዝር የሚጻፍ ይሆናል።

ለውድ ባለቤቱና ለእህቱ ቤተሰብና ዘመድ ጽናቱን እንዲሰጣቸው ጸሎታችን ነው።

**ወገኖቹ የ ኢ.ኢ..ድ.ኤን አባሎች**







## ወንድም ወልደአማኑኤል

**1938 - 2001**

# ዓርባ ቀን መታሰቢያ



**የወንድም ወልደአማኑኤል
አጭር የሕይዎት ታሪክ**

## የማይሞት ሰው ሞተ

አቶ ወንድም ወልደአማኑኤል ለኢትዮጵያ አገራቸ ው የሰጡት ልባዊ አገልግሎትና እሳቸውንም በአካል የሚያ ውቅ ሰው በዘመናት አንድ ጊዜ ብቅ ብለው ከሚታዪ አገር ወዳድ ሰዎች ውስጥ እሳቸው አንዱ መሆናቸውን አይጠራ ጠሩም፡፡

አቶ ወንድም በሰኔ 12 ቀን 1938 ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ ወልደአማኑኤል አበበና ከእናታቸው ከወይዘሮ አሰለ ፈች ተሰማ አዲሰ አበባ ከተማ ተወለዱ፡፡ ዕደሚያቸው ለት ምህርት ሲደርስ አዲስ አበባ ውሰጥ በሚገኘው በቀ.ኃ. ሥ. ኮከበ ጽብሃ ትምህርት ቤት የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ት ምህርታቸውን ተከታትለው አጠናቀዋል፡፡ የከፍተኛ ትምህ ርታቸዉን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተከታትለው የመጀመሪ ያ ድግሪያቸውን (ባቺላርስ ኦፍ አርት) አግኝተዋል፡፡ ከዚያ ም በትምህርት ሚኒስቴር የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤት በአስተዳደር ዘርፍ ተቀጥረው በቅንነትና በታ ታሪነት ሰርተዋል፡፡

አቶ ወልንድም ወልደአማኑኤል ከልጅነት እስከ እ ውቀት ለተጎዳ አዛኝ፣ ለጓደኞቻቸው አለኝታና መከታ፣ ለአ መኑበት በፍጹም የሚቆሙ አይበገሬ ግለሰብ ነበሩ፡፡ ፍትሕ ሲዛባ፣ አድሎ ሲደረግ በገሃድ ቆመው የሚጋፈጡ ልበሙሉ እንደነበሩ አብሮ አደግ ጓደኞቻቸው ይናገራሉ፡፡

አቶ ወንድም የተወለዱት ኢትዮጵያ አገራቸው የለ ውጥ ታጋዮችን በምትሻበት ዘመን ነው፣ ሰለሆነም አገራቸ ውን በዕድገት እንድትገሰግስ ፣ ሕዝቡ በዕውቀት እንዲዳብ ርና በሀብት እንዲበለጽግ በተደረገው የትግል እንቅስቃሴ የዩኒቨረስቲ ተማሪ በነበሩበት ጊዜ በግንባር ቀደምትነት ተሳትፈዋል፡፡ በስራ መሰክ እያሉም ትግላቸውን ቀጥለውበ ታል፡፡ ወታደራዊዉ መንግስት በየጊዜው በታጋዮች ላይ ሲያደርስ በነበረው ወከባና ግድያ ሳይደናገጡ በአላቸው ሃይል ሁሉ ትግሉን ሲያራምዱ ቆይተው ሁኔታው በተጣበበ በትና ከፍተኛ መስዋዕትነት በጠየቀበት ጊዜ አቶ ወንድም አዲስ አበባን ለቀው ወደ አሲምባ ተራራ ገቡ፡፡

የሚያስፈልገውን ወታደራዊ ስልጠና ከአጠናቀቁ በ ኋላ በቆራጥነት ለመስዋዕትነት ተሰለፈዋል፡፡ በጊዜው በኃይ ል ውስጥ በኮሚሳርነት ተመድበው ታግለዉ አታግለዋል፡፡

## ለወድም ወልደአማኑኤል

**ማስታዎሻ**

በዘውገ ፋንታ

ምን እንበል ዛሬ?
ምን እንበል ነገ?
የሚለው አገሬ!
ጥሎን ከአረገ።

ፈሪ አትበሉ፣
ደክሞ የተኛውን፣
ይነሳል አካሉ፣
ብጠሩ ሀገሩን።

እሱ የሚወደው፣
ጦብያ ሲባል ነው።

ባውቅበት ማልቀስ!
መፈክር ቢቀናኝ!
እል ነበር ድረስ!
ጀግና ሆይ ስማኝ!
ሲበቃህ በቃኝ።

የጠፋውን ወጥቶ፣
ፈልጉ አትበሉ፣
ያረፈውን መሽቶ፣
አልፎ ያንን ሁሉ፣
ቅዱስ ቀን ጠፍቶ፣
ምን ይሁን በዐሉ?
እሑድ ጠፋ ካሉ!

አሻፈረን እንበል!
እሱ አይመራንም!
መንገዱን ስተሀል፣
አንተም የኛ ወንድም።

መለስ በል ሂደሃል፣
አንልም በቅቶሃል።



በዚህም ምክንያት በብዙ የኢትዮጵያ ጥያቄዎች ላይ ከወንድ
ም ጋር ተቃራኒ አቋምና አመለካከት የነበራቸው ቡድኖችና ግለሰቦች
ርሱን አባብለውና ደልለው ወደራሳቸው ጎራ ለማስገባትና ለማስጠጋ
ት ይጥሩ እንደነበር የሚታወቅና የሚታወስ ነው ። ይሁን እንጂ ያደ
ረጉት ተደጋጋሚ ሙከራና ጥረት ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ልክ እንደ
ቁሳቁሳዊ ይዞታውና ንብረቱ ረቂቅ ሀብቱም (እዉቀቱና ችሎታው)
ቢሆን የብዙሃንን ደህንነትና ፍትህን የሚረዳ ሳልመሰለው አቋም መደ
ገፊያና መሳሪያ እንዲሆን አልፈቀደም። አልተባበረም።

ለዚህ ነው ከራሳቸው ፤ ከጌቶቻቸውና ከቡድናቸው ጥቅም
አንፃር ተንደርድረው የኢትዮጵያን ብዙሃን ትግልና መብት የሚያድ
በሰብሱና የሚፃረሩ ሁሉ የውንድም ብዕርና አንደበት እጅግ ይለበልባ
ቸውና ይኮሰኩሳቸው የነበረው።

ይህንኑ ለመመዘንና ለማረጋገጥ ከወንድም ጋር ይለዋወጧቸ
ው የነበሩትን መልሶችና አስተያየቶች ወደ ኋላ ዞሮ አየት መልከት
ማድረግ ብቻ ነው።

የወንድም ጀግንነትና ደግነት ተዘክሮ ፤ ተዘርዝሮና ተለቅሞ
የሚያልቅ አይደለም። መላው ሕይወቱ በደግነትና በጀግንነት የታነፀ
ና የተመላ ስለነበረ ።

በየቦታውና በየጊዜው ለመብት ፤ ለፍትህና ለሰው ልጅ ደህንነ
ት በሚደረግ ጥረትና ሂደት ላይ በፈቃደኝነት ከራሳቸው ድርሻ በላይ
ኃላፊነት የሚሸከሙ ግለሰቦች፤ ቡድኖችና ትውልዶች እንደተወርዋሪ
ኮከብ ብቅ ይላሉ (ይፈጠራሉ)። ከሽክማቸው ክብደት የተነሳ ብዙውን
ጊዜ ከሁሉ በፊት ተዳክመውና ተሰባብረው ይወድቃሉ ።

ወንድም ኮስታራና ቆራጥ የነፃነት ፤ የመብትና የፍትህ አርበ
ኛ ነበር። በቋሚነትና በዘላቂነት። እስከ መጨረሻው ። በቆመበት
መስመርና እምነት ማትቡን ሳይበጥስ ተሰናበተ ።

በሞቱ ዋዜማ ደውሎ ካነጋገራቸው ጓዶቹና ወዳጆቹ ጋር አ
ጭር የሰላምታ ልውውጥ ካደረገ በኋላ ፈጥኖ (እያቃሰተ) "ኢትዮጵያ
እንዴት ነች/ ያገራችን ፖለቲካ ወዴት እየመራ ነው?" ብሎ ጠየቀ
። ዕረፍት አድርግና በሌላ ጊዜ እናወራዋለን ተብሎ ጥያቄው ተቀ
ጨ። ለጥያቄው መልስ ለመስማት ሳይመለስ በዚያው ሄዶ ቀረ !!!



በዚህ ሀላፊነታቸው የጓዶቻቸውን ንቃትና ተሳተፎ በማጠና
ከር ረድተዋል። ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ አስፈላጊ ስ
ብሰባዎችን በመጥራትና በመምራት ተካፍለዋል። ሰራዊቱ
በአካሄዳቸው ፍልሚያዎች ተሳትፈዋል። የትግል ሰማቸ
ው ታፈሰ በመባል የታወቁ ነበር።

አቶ ወንድም ሰራዊቱ ወደ በጌምድር በተሻገረበት
ጊዜ ወደ ሱዳን በመውጣት ትግላቸውን ቀጥለዋል። በሱዳን
ቆይታቸውም ከሜዳም ሆነ ከአገር ቤት እየተሰደዱ የሚ
መጡ ኢትዮጵያዊያንን በማቋቋምና አገሩን በማለማመድ
ይረዱ ነበር። እየሰሩ ያገኙትን ደመወዛቸውን ከስደተኞች
ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጋር የሚካፈሉ ሩሩህና ደግ
ሰው ነበሩ። የሱዳን መንግስት በስደተኞች ላይ ምክንያት
እየፈጠረ የሚያደርሰውን ማንገላታት ለተባበሩት መንግሰ
ታት በማመልከት የታሰሩት እንዲፈቱና ሁሉም ስደተኛ
የስደተኛ መብቱ እንዲከበር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጉ
እንደነበር አብረዋቸው የነበሩ ጓደኞቻቸው ይናገራሉ።

በመስከረም ወር 1973 ዓ.ም ወደ አሜሪካ ተጓዙ ።
አሜሪካም ከመጡ በኋላ ትምህርታቸውን በመቀጠል ሎስ
አንጀለስ ከሚገኘው ካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ በንግድ
አስተዳደር (ቢዝነስ አድሚኒስትሬሺን) በድግሪ ተመርቀዋ
ል። በ1976 ዓ.ም ከውድ ባለቤታቸው ከወይዘሮ ሄለን ወል
ደአማኑኤል ጋር ተጋቡ ። አቶ ወንድም ሎስ አንጀለስ ውስ
ጥ ለሆም ሴቪንግስ ኦፍ አሜሪካ ይሰሩ ነበር። በስራቸዉ
ላይ ባሳዩት ታታሪነተና ችሎታ የድርጅቱ ረዳት ፕረዘዳን
ት ሆነዉ ሲሰሩ ቆይተዋል። ከዚያም በ1992 ዓ.ም ከባለቤ
ታቸው ከወይዘሮ ሄለን ጋር ሆነው የመኖሪያ ቦታቸውን
ወደ ዋሺንግተን ስቴት በማዛወር በግል ስራ ላይ ተሰማርተ
ው ይኖሩ ነበር።

በነበራቸው ከፍተኛ የሐገር ፍቅር በግል ስራ ተሰማር
ተውም ትግላቸውን አላቋረጡም። ዘመኑ በፈጠረው ድረገጽ
(ኢንተርኔት) ግንባር ቀደም በመሆን ስለአገራቸው ጽሁፍ
ና ትንታኔ አቅራቢ ነበሩ። በሚነሱ የአገር ጉዳዮች ላይ
ሳይሰለቹ ገንቢና አታጋይ ጽሁፎችን ያዉጡ ነበር። ዋና
ዋና የሐገር ጉዳዮች ላይ ምላሺ በመጻፍ አቶ ወንድምን
የማያስታውስ አለ አይባልም።

አቶ ወንድም አገራቸውንና ቤተሰባቸውን የሚወዱ፤
ለትዳራቸው ታማኝ ፤ ትሁትና ታላቅ ሰው ነበሩ።

አቶ ወንድም ወልደአማኑኤል በአደረባቸው የልብ
ህመም ምክንያት በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ዋሺንግተን ሕክምና
ሲደረግላቸው ቆይተው በተወለዱ በ62 ዓመታቸው መስከረ
ም 12 ቀን 2001 ዓ.ም አረፉ። ቸሩ እግዚአብሔር ነፍሳቸ
ውን ይማር።

**ባለቤታቸው ወ/ሮ ሄለን ወልደአማኑኤል**
**እህታቸው ወ/ሮ ሃና ወልደአማኑኤል**

**እንዲሁም የት/ቤትና የትግል የቅርብ ጓዶቻቸው።**



## ወልደሺ ተኪ ኢትዮጵያ

### ከወንድሙ መኮንን

እኔስ እንደማልቀስ አንጎራጉራለሁ

ጌታን አልጋፋ ሌል ምን እላለሁ፤

እህህን በሆዴ፤ እህህን በአንጀቴ አመላልሳለሁ

የዘፋኙን ቅኝት እደጋግማለሁ።

"ሞት እንኳን ጨክኖ፤ ወስዶ ከሚያስቀር

ምን አለ ደጋጉን፤ ዳግመኛ ቢፈጥር።"

ላይመለስ ሂዷል፤ በር ደጃፉን ከፍቶ

እንዲያው ጎርደድ፤ ጎርደድ

መሄድ አለመሄድ

አንዴ ወዲያ ወልሺ፤ አንዴ ወዲህ ወልሺ

ተስፋ መቁረጥ መጣ ያ ውቃቢ የለሺ

ተብረከረከብኝ ለገመ ጉልበቴ

ራደ ራደ ሆዴ፤ ተናወጠ አንጀቴ

መለየቱን አውቆ ዛለ ሰውነቴ

አምጠሺ አምጠሺ ወልደሺ ተኪ እናቴ

ባዶነት ተሰማኝ ወንድም በማጣቴ

**ለወንድም ወልደአማኑኤል**
**መታሰቢያ**

BUCKINGHAM, ENGLAND, 26 SEPTEMBER 2008



## የሁሉ የነበረ ሰው/ የሁሉ ሰው ወንድም አረፈ

### ከአቶ ገብሩ ገብረወልድ

ወንድም ወልደአማኑኤል ሁሉን በወንድምነት በህትነትና በእኩልነት ዓይን የሚያይ ሰው ነበር፡፡ የወንድም አይነ ሕሌና ሰውን በዘርና በቀለም፣ በእምነትና በሐይማኖት ወዘተ ለይቶ የማዬትና የመስፈር ችሎታ አልነበረውም፡፡ የወንድም ዓይነ ህሊና አብርቶና አተኩሮ የሚመለከተው ሰው መሆንን ብቻ ነው/ነበር፡፡ የሰው ሁሉ አንድና እኩል መሆንን ብቻ ነው/ነበር፡፡

እጅግ ሰባዊና ርህሩህ ከመሆኑ የተነሳ የሌላን ችግር እንደራሱ ችግር በማየት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የተቸገረን ከመርዳት የተቀጠበበት ጊዜ ተፈልጎ አይገኝም ፡፡ ሁሉም ባይሆን አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች በመጠኑም ቢሆን በየጊዜው የተቸገረን ሲረዱ ይታያሉ ፡፡

የወንድም በጎ ተግባርና ርዳታ ግን ምንጊዜም የማይቆምና የማይቋረጥ በቦታና በጊዜ የማይገደብ ቋሚ ሂደትና ክስተት ነበር፡፡

በዚህ ምክንያት የወንድም ቸርነትና ደግነት በአቅሙ ቁና የተለካና የተሰፈረ አልነበረም፡፡ ያለውን ገንዘብና ንብረት ለተቸገረ አከፋፍሎ በየጊዜው ራሱን በችግር ላይ ይጥል እንደነበር በተለያየ ጊዜና ቦታ የሚያውቁት ሁሉ በአንድ ድምጽ ይመሰክራሉ፡፡

እናም ወንድም ሰውን እንደራሱ የሚወድ ብቻ አልነበረም፡፡ ሰውን ከራሱ አብልጦ የሚወድ እንጅ፡፡

እንደዚሁም ወንድም ምንጊዜም ቢሆን የራሱን መብት ላለማስነካትና ላለማስነጠቅ በቀናኢነትና በቁርጠኝነት ሲከላከልና ሲታገል ኖሯል፡፡ በኃይስላሴ ዘመን ኢትዮጵያ ዓይን ሲታይና ሲመዘን ወንድም የተደላደለና የተቀማጠለ ኑሮ ነበረው፡፡ ይሁን እንጅ መላው የኢትዮጵያሕዝብ ለዘመናት አስሮ ያቆዬውን የባርነትና የጭቆና ስርዓት ለመንቀልና ለመገርሰስ ሲነሳ ወንድም ፈጥኖ ከአገሩ ሰፊ ሕዝብ ጋር ተቀላቀለ ፡፡ የኑሮ መሳዮቹንና ቡድኖቹን ከድቶ ከብዙሃን ወገኖቹ ጋር ወገነ ፡፡ በኢትየጰጅያዊያን መካከል ወንድምማችነትና እኩልነት እንዲኖር በፍትሕ ላይ ለሚመሰረት ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስርዓት ለመታገልና የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጦ ተነሳ፡፡

መጀመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ በሕቡዕ፣ ከዚያም በሰሜን ኢትዮጵያ በትጥቅ ትግል ተሳተፈ ፡፡

ብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታጋዮች ከትግል ሜዳ ወጥተው መጀመሪያ በጎረቤት አገር (ሱዳን) ቆይተው በየአገሩ መሰራጨታቸው ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ ወንድም ወልደአማኑኤል ወደ አሜሪካ ከዘለቁት መካከል አንዱ ነው/ነበር፡፡

የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል ለማጠናከርና ለማስተሳሰር በተደረጉ ጥረቶች ሁሉ ያለማቋረጥ ሲሳተፍና ሲከታተል ቆይቷል፡፡ ሌላው ሁሉ ቢቀር አንገብጋቢ በነበሩ/በሆኑ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ በተካሄዱ ውይይቶችና ክርክሮች ወንድም የነበረውን ንቁህ ተሳትፎና ያበረከተውን አስተዋፅዖ ለመገንዘብና ለመመዘን ወደኋላ ዞር ብሎ የኢትዮጵያዊያን ድህረገጾችን መመልከትና ማስታወስ ብቻ ይበቃል፡፡

ወንደም ጥልቅ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ዕውቀት፣ ግልጥና የሰላ ያቀራረብ ችሎታና ስልት ነበረው፡፡

አንድን ርዕስ ተንትኖ ፣ አበጥሮና አብርቶ የራሱን አቋምና አስተያየት ለይቶ የማሳየት ችሎታውና ተሰጥዖው ሁሉንም የሚያስደንቅ ነበር፡፡ ተቃዋሚዎቹንና ታቃራኒዎቹን ጭምር፡፡